# <u>አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል</u>

እንደሚታወቀው በኮሎኔል ደመቀ የተቀጣጠለውን "የአማራ የማንነት ጥያቄ" ሕዝቡ በራሱ ተነሳሽነት ደሙን እያፈሰሰና ከትግሬ ወራሪዎችና ፋሽሽቶች ጋር ግብ ግብ በገጠመበት ወቅት ቀደም ሲል ይዟቸው ከወጣው መፈክሮች አንዳንዶቹን ለላሙና ብንጠቅስ (1ኛ) ወልቃይት አማራ ነው (2ኛ) የሻዕቢያ ተላላኪ ህዋሃት(ወያኔ) እንጅ ወልቃይት አይደለም (3ኛ) የኦሮሞ ወገኖቻችን ደም የእኛ ደም ነው ወዘተ የሚሉ ይገኙበታል። ቀጠል አድርጎም ሻዕቢያንም ሆነ ወያኔን የአማራ ሕዝብ እንደማይፈልጋቸውና እንደሚታገላቸው አብስሯል ።

በማከታተልም የአማራን ማንነት የሚፈታተን፣የሥርጎ ገቦች መፈክር " አሸባሪው ወያኔ እንጅ <u>ግንቦት ሠባት</u> አይደለም " በማለት ተሰማ።ይህ ሆን ተብሎ የተቀነባበረ የኢሳት ተግባር፣በአማራው ቁሥል ላይ ጋሬጣ እንደመሥደድ ይቆጠራል።

ለማንኛውም እሥከ ህዳር 8ቀን የተሠራውን አይቼ እንዳላየሁ፣ሰምቼ እንዳልሰማሁ ባልፈው ይሻላል የሚለውን ውሳኔ በመውሰድ ፅሁፌን ከመፃፍ ተቆጠብኩ።

ምክንያቱም የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔ ውሸት ሥላንገሸገሸው፣የወያኔን ቴለቪዥንም ሆነ ራዲዮ ላለማዳመጥ ወስኖ፣ አማራጭ አድርጎ የወሰደው ኢሳትን ሥለነበረ እና እኛም ደግፈነው ሥለነበር ነው።

ይህ በዚህ እንዳለ የአማራውን ትግል ለግንቦት ሰባት ለማሥረከብ የተለያዩ የማራቶን መንገዶች ታቀዱ፣

(1ኛ) ብርሀኑ ወጥቶ ከሕዝቡ መካከል ነን እንዲል ተደረገ፣

(2ኛ) ቅማንቱ ዓለም አንተ ገብረስላሴ (ፕሮፌሰር) ከብርሀኑ ጋ ሥለሚሠራ በጎንደር ህብረት አማካይነት ገንዘብ ሠብስቦ በእርዳታ አሥመስሎ ጎንደር ላይ ዘመድ ፈልጎ በመስጠት አማራ ሳይሆን በጎንደሬነት እንዲሰባሰቡ እየሞከረ ነው።

ቃለመጠይቅም ሥለሰጠ አድምጡት።እንደሱ ፍላጎት የጎንደር ሕዝብ የአማራ ማንነት ካባውን አውልቆ የጎንደሬነት የጎጥ ካባ ከለበሰ በኋላ ግንቦት ሰባትን እንዲደግፍ ማድረግ ነው።
ለዚህም ነው ዋልድባ ውሥጥ ካህናቱ ጭምር ሲወናበዱ የታዩው።ይህ ሠው የአማራውን ማንነት በገንዘብ ሊያጠፋ የሚታገለው፣በቅማንትነቱ ነው ወይስ ከብርሀኑ ጋ በመቆሙ፣ወያስ በሁለቱም? እሱ ራሱ ነው የሚያውቀው።

(3ኛ) በአንድ ጎኑ ኤርትራዊ የሆነው በጎጃሜነት የሚታወቀው ብርሀኔ መዋ ደግሞ ከብርሀኑም ጋር ሥለሚሠራ አሁን የአማራው ትግል ሲፋፋም በደመነፍስ ተሯሩጦ የጎጃም ሕብረት(ማሕበር) ፈጠሮ የአማራን ማንነት አጥፍቶ በጎጃም ጎጠኝነት ሊተካ እየተሯሯጠ ይገኛል።ሕዝቡን ከቻለ በጎጃሜነት ካሰባሰበ በኋላ ለብርሀኑ ለማስረከብ ነው። እንኳን የኤርትራ ዘር ኑሮት ይቅርና ከአማራ ብቻ የተወለዱት አይደሉም እንዴት ላይ ታች እያሉ ወገናቸውን የሚያጠፉት።

(4ኛ) ሆላንድም፣እንግሊዝም ሆነ አሜሪካ ወዘተ የሚገኙት ኢሳቶች የገንዘብ ምንጫቸው (ደመወዛቸው) ብርሀኑ እንደሆነና እሱም ከዬት እንደሚያገኘው ያደባባይ ምሥጥር ነው ካላላችሁ በሥተቀር አባላቱና ደጋፊዎቹ ጠይቁት። ከኢትዮጵያኑ ወገን የሚገኘው ሙሉ በሙሉ ዜናውን እንኳን ለማስተናገድ አይችልም።ከተለያየ አቅጣጫ ለሚያገኙት ገንዘብ ሽፋን ቢሆን እንጅ።

ይህ በዚህ እንዳለ፣ይግረማችሁ በሚል በብርሀኑ የዜና ማእከል በሆነው ኢሳት ማክሰኞ በነጮች ህዳር 8ቀን 2016 ዓም ደግሞ ፀረ-አማራ የሆነው የአገው ተወላጅ ፋሲል የኔዓለም የአርበኞች ግንቦት ሰባት

ጎንደር ውስጥ እንዳለ አድርጎ ጠቅሷል።እነኚህ የውሸት ቋቶች ውሸት አያልቅባቸውም በማለት ከመገረም አላለፍኩም።

ኤርትራ ውስጥ ትናንትም ዛሬም የገቡ ኢትዮጵያውያኖች፣በሻዕቢ ቁጥጥር ሥር እንዳሉ እናውቃለን።
-ዛሬ ብርሀኑ ነጋ ሻዕቢያን የንፍስ አባት አድርጎ እዋጋለሁ እያለ በየዋሁ አማራ ሥሜት ቁማር እየተጫወተ፣እያዘናጋና ገንዘብ እያሥከፈለ አንዲትም ጥይት እሥከዛሬ አላሥጮኸም።እሥካሁን በዚህ መጣሁ፣ተኮስኩ፣ወያኔዎችን ጎምጎፋ ላይ፣በጎንደርም በወልቃይትም ወዘተ ድባቅ መታሁ፣ገደልኩ እያለ በሬ ወለደን ሲያዘምርብን ይኸውና ዓመታት ተቆጠሩ።
የሌለበትን አለሁ እያለ ለወያኔ ዱላ እያቀበለ በሽብርተኛ ሥም ሕዝቡን ያሥደበድባል። እንደርሱ ከሆነ ወያኔዎችን ዱሮ ዱሮ ነው የጨረሳቸው። የጨረሳቸው ወያኔዎችም ከመቃብራቸው ተነሥተው መጥተው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከአማራ ሕዝብ ጋር ይታኮሳሉ።
-በባህር ዳር 49 አማሮች በትግሬ ወራሪዎች ሲገደሉ፣አንዲት እናት "ከበርሀ ያላችሁ ድረሱልን፣ መሳሪያም ሥጡን" ብላ ሥትማፀን ከብርሀኑ ጭምር ያልሰማ የለም። እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል ነውና ሲዋሽ የኖረው ግንቦት ሰባት ቢኖር ኖሮ  "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ" እንደተባለው በዚህ ጊዜ ከተፍ ይል ነበር።
ከእንግዲህ አማራው እርሙን አውጥቶ ራሱን በራሱ ነፃ ከማውጣት ውጭ የሌለ ኃይል እንደማይጠብቅ ግልፅ ሆኖለታል።በአማራ ሕዝብ መራራ ትግል መቀለድና ሳይታገሉ በወሬ ድል መጎናፀፍ አይቻልም።

ኢሳትም በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እያገኘ መሄዱን ሥላወቀና ሥላረጋገጠ፣"ውሻ በበላበት ይጮሀል "እንደሚባለው፣ብርሀኑን ከገባበት የውርደትና የወሸት ረግረግ ለማውጣት የአማራውን ትግል የግንቦት ሰባት እንደሆነ በማሥመሰል የአማራን ተጋድሎ ከፋኝን "የነፃነት ኃይሎች" በማለት  በአማራው ትግል ላይ ውሀ ሲቸልስ ተሥተውሏል። ኢሳት ለብርሀኑ ጥብቅና በመቆሙ በአማራነት የሚደራጀውን ኃይል በረቀቀ መንገድ ለብርሀኑ ለማሥረከብ ሲጥር ይታያል።

ዛሬ የመገናኛ ብዙሀኖች ለግንቦት ሰባትና፣በውጭ ለሚገኙ ተገንጣይ ቡድኖች ሰፊ መድረክ እየሰጡ፣ በውጭ አገር የአማራውን ብሶት ሊያሥረዱ የሚችሉ የፖለቲካ ተመክሮና ዕውቀት ያላቸውን አማሮች በረቀቀ መንገድ ያርቃሉ።ካቀረቡም  "እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው" ዓይነት የረቀቀ ተፅዕኖና ማዕቀብ የማድረግ  ባህል ተጠናውቷቸዋል።

በቪኽን ኢትዮጵያ ተብዬው፣የግንቦት ሰባት ነዓምን ዘለቀ የተባለው ግለሰብ፣ "ኢትዮጵያ የምትባል አገር እና የኢትዮጵያ አንድነት ብቻ ሲባል ስፎኬት(ያፍነዋል) ያደርገኛል" ሲል ተደምጧል። ሌንጮ ለታም ከወያኔ ጋር ኢትዮጵያን የገነጠለውን ህገ መንግሥት ያወጣ ነው፣አሁንም ውስጡ አነግ፣ላዩ አስመሳይ ና አታላይ ዴሞክራት፣እኛን መናጆና አጃቢ አድርጎ የበለጠ ለመበጣጠስ የመጣ እንደሆነ ይግባን።
ሌንጮ ባቲም  "ኢትዮጵያዊነት አለወይ፣የለም " ብሎ አፉን ሞልቶ የሚናገር ነው።እነብርሀኑ ለሚደግፏቸው ተገንጣይ ቡድኖች አማራውን የሥልጣን መረማመጃያና የህልውናው መጥፊያ ማድረግ ነው። እነኚህን ኢትዮጵያን የከዱ ሰዎች አቅፎ ነው "ግንቦት ሰባት ነን፣ እንዋጋለን" እያሉ፣ከብዙሀኑ የዋህ አማራ ገንዘብ እየወሰዱ በም ዕራቡ አማላጅነት ሊወድቅ ከሚንገዳገደው ከነፍሰ ገዳዩ ወያኔ ጋር ሥልጣን ለመቀራመት ላይ ታች ሲሉም የሚሥተዋሉት። በአጭር አነጋገር ወያኔ እንዳይወድቅ ገፀ በረከት እየሆኑለት ነው።
 ሥለዚህ አማራ ሆነህ  በብርሀኑ በኩል መፍትሄ አገኛለሁ ብለህ የምታሥብ ወገኔ፣እሥከዛሬ የተሰራብህ ሸፍጥ ይብቃ።
ከዛሬ ጀምሮ አገር አጥፊዎችን ሳይሆን ዘርህን ወገንህን አማራውን ደግፍ፣ነገ አፍንጫህን ላስ ከሚሉህ ጋ የመቆሙ አደጋ ከፍተኛ ነውና።

የኢሳትም ሆነ የግንቦት ሰባት ደጋፊዎች ነን የምትሉት ራሳችሁን መጠየቅ ያለባችሁ አንድ ነገር አለ ይኸውም፣በአሜሪካ፣በለንደንና በሆላንድ ወዘተ የሚሠሩት  የኢሳት ሰራተኞችና ብርሀኑ ዜናውን የሚያሥተላልፉበት እና ደመወዛቸው ከየት ይመጣል ብላችሁ ጠይቁ፣ራሳችሁን አሠሩት?ይህ ከሕዝብ

የሚዋጣው ከእነታማኝ ደመወዝ እሥከ ብርሀኑ ይበቃል?አይበቃም ነው መልሱ። ከሕዝብ የምትዋጣው ለማስመሰልና ለማሟያ ነው። ለዚህ ሁሉ ወጭ መሠረቱ ብርሀኑ ነው።እሱ ደግሞ ከየትኞቹ አገሮች እንደሚያገኝ(ኤርትራ ለማለት እንዳልሆነ ተረዱኝ) ከተገደድን ወደፊት እናወጣዋለን።ለዛሬ ግን በዚሁ እንግታው።ለዚህ ነው አር ዕስቱን "አሳ ጎርጓሪ  ዘንዶ ያወጣል" ያልነው።

እናንተ የአማራ ወገኖች! ነገ ከእነሌንጮና ከእነብርሀኑ ጋር ያለው ጋብቻ መፍረሱ ሥለማይቀር፣በቅርብ ወገኖቻችሁ በዶክተር አቤል ዮሴፍ፣በወንድም የሺጥላ፣በእህት ርሥቴ ወዘተ ላይ የምታደርጉትን ዘለፋ ብትተውት ይመረጣል።የሚያሥገምተው ራሳችሁን ነው።
እንዳለመታደል ሆኖ ከጥንት ጀምሮ በተለያዩ ድርጅቶች እየገባን እርስ በእርስ ሥንተካተክና ስንጋደል የኖርነው እኛው አማሮች ነን።ዛሬም አማራ ብለን የተነሳነው በአንድ በኩል፣ኢሳትና ግንቦት ሰባት (ብዙው  አማራ ነው፣ወደወገንህ ና) በሌላ በኩል ሆነን ሥንተካተክ ጠላት በመካከላችን እየገባ ደስታውን ያበሥራል።

እሥከዛሬ ድረስ የፖለቲካ ባህላችን በአመራር ላይ ያሉ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን "ልጅን ከወደዱ ከእነለሀጩ ነው" እንደሚባለው፣ያላንዳች ጥያቄ መቶ በመቶ በጭፍን ደግፎ  መከተል ነው። በተማሪው እንቅስቃሴም ብሎም በኢሕአፓና በመኢሶን፣ በቅንጅትም ሆነ ዛሬም የምንጠቀምበት መንገድ በሀሳብ ልዩነቶች ዙሪያ በጥሞና ተነጋግሮ ዕውነቱን ተረድቶ፣የሚነቀፈውን ነቅፎ ድጋፍን ለመሥጠትም ሆነ ለመንሳት ሲቻል ሁሉንም ነገር የጨረባ ተሥካር ማድረግና የወያኔን ሥራ መሥራት ተገቢ አይደለም እላለሁ። እነኚህ  እነ እርስቴን፣እነሄኖክ የሺጥላን፣እነዶክተር አቤል ዮሴፍን ወዘተ የመሳሰሉትን የዕውነት ሰዎች መከራከሪያ ነጥብ ይዛችሁ ከመከራከር ይልቅ በጠረባ አማራውን አንገት እናሥደፋለን ብላችሁ ከሆነ አትልፉ።ከ40ዓመት በላይ የተሄደበትና ውጤተቢስ የሆነ የትግል መንገድ ነው።

**ኃይሉ በላይ**